መልእክት አምስት

## ከአማሌቃውያን ጋር ጦርነት

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ 1 ሳሙ. 15፤ ዘጸ. 17፡8-13፤ ገላ. 5፡16-17፣ 24

### I. አንደኛ ሳሙኤል 15 ሳኦል አማሌቃውያንን አሸንፎ ሲይዝ ያለመታዘዙ ዘገባ ነው፦

ሀ. ሳኦል ጠላትን አሸነፈ፣ ሆኖም ግን እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ አልታዘዘም—ቁ. 7-9።

ለ. እዚህ ላይ ሳኦል ፈጽሞ፣ ሙሉ በሙሉ ተጋለጠ፣ ከዚያም በእግዚአብሔርና በሳሙኤልም አሳልፎ ተሰጠ—ቁ. 14-26።

ሐ. ይህ ምዕራፍ ዛሬ ለእኛም አስፈላጊ ትምሕርትን ይዟል።

### II. በምሳሌ አማሌቃውያን *ሥጋን*—የወደቀውን ሰው—ያመለክታሉ—ዘጸ. 17፡8-16፦

ሀ. ከጌታ ጋር መቀጠላችንን በማስተጓጎል አማሌቅ፣ *ሥጋ*፣ ቀንደኛ ጠላት ነው—ቁ. 8፤ ዘዳ. 25፡17-18፦

1. *ሥጋ* ጦርነት ወዳድ፣ አጥፊ እና የሚያውክ እንደሆነ በማሳየት አማሌቅ የሚለው ስም "ጦርነት ወዳድ" ማለት ነው።
2. የክርስቲያንን ሕይወት የሚያጠፋው እጅግ ትልቁ አጥፊ *ሥጋ* ነው—1 ጴጥ. 2፡11።
3. እግዚአብሔር ከአማሌቅ ጋር የማያቋርጥ ጦርነት የመዋጋቱ ሃቅ እግዚአብሔር *ሥጋን* እንደሚጠላ እና *ሥጋን* ማጥፋት እንደሚፈልግ ይገልጣል—ዘጸ. 17፡16፤ ገላ. 5፡17።

ለ. *ሥጋ* የወደቀውን አሮጌውን ሰው ጥቅል ድምር፣ መላው የወደቀውን ማንነታችንን ያመለክታል—ዘፍ. 6፡3፤ ሮሜ 7፡18፤ ገላ. 2፡16፦

1. *ሥጋ* የአሮጌው ሰው ከውስጥ ወደ ውጭ መኖር እና የአሮጌው ሰው መገለጥ ነው—ሮሜ 6፡6።
2. *ሥጋ* ከእግዚአብሔር ጋር ጠላት ነው፣ *ሥጋ* ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛም፣ እና *ሥጋ* ራሱን ለእግዚአብሔር ሕግ ሊያስገዛም አይችልም—8፡7።

ሐ. *ሥጋ* የእግዚአብሔር ጠላት መሰባሰቢያ ነው፣ ለሥራውም እጅግ ትልቁ ማዕከል ነው—ገላ. 5፡19-21፦

1. በመላው አጽናፍ-ዓለም ውስጥ የእግዚአብሔር ልዩና ብቸኛ ጠላት፣ ተግባራዊ በሆነ መልኩ፣ ሰይጣን ሳይሆን *ሥጋ* ነው—ሮሜ 8፡7።
2. *ሥጋ*፣ የወደቀው ሰው፣ ከሰይጣን ጋር ሙሉ በሙሉ አንድ ነው፣ እግዚአብሔርንም ለመዋጋት ሰይጣን ይጠቀምበታል—ማቴ. 16፡23፤ ገላ. 5፡17።
3. እኛን በመዋጋት ኃጢአትን፣ ዓለምን እና ሰይጣንን በመቅደም ከጠላቶቻችን መካከል *ሥጋ* ቀዳሚው ነው—ሮሜ 8፡3።
4. እግዚአብሔር ሰይጣንን በሚጠላበት በዚያው ልክ *ሥጋን* ይጠላል፣ ሰይጣንን ሊያጠፋው በሚፈልግበት በዚያው ልክ *ሥጋንም* ማጥፋት ይፈልጋል—ዘጸ. 17፡16፤ ዘዳ. 25፡17-19፤ 1 ሳሙ. 15፡2-3።

መ. በአማሌቅ ዘንድ የጌታን ዙፋን የሚቃወም እጅ አለ—ዘጸ. 17፡16፤ 1 ሳሙ. 15፡22-23፦

1. ልክ ሰይጣን በሆነ ጊዜ ሊያደርግ እንደሞከረው እንዲሁ አማሌቅ የእግዚአብሔርን ዙፋን ለመገልበጥ ሞከረ—ዘጸ. 17፡8፣ 16።
2. ልክ እንደ ሰይጣን *ሥጋ* የእግዚአብሔርን *ሥ*ልጣን ይጻረራል—ኢሳ. 14፡12-14፦
   ሀ. *ሥጋ* በእግዚአብሔር ላይና በዙፋኑ ላይ ያምፃል።
   ለ. እግዚአብሔር በአገዛዛዊ አስተዳደሩ የሚያደርገውን ነገር ሁሉ *ሥጋ* ይቃወመዋል።
3. *ሥጋችን* የእግዚአብሔር *ሥ*ልጣን ጠላት ነው፣ በእግዚአብሔር አገዛዛዊ አስተዳደርም ላይ ያምፃል፦
   ሀ. *ሥጋ* እጅጉን አስቀያሚ ነው፣ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ዙፋን፣ አስተዳደር እና ዕቅድ ይጻረራል—ራእ. 4፡2፤ 5፡6፤ ኤፌ. 3፡11።
   ለ. የ*ሥጋችን* እያንዳንዱ ገጽታ፣ መልካም ሆነ ክፉ፣ የእግዚአብሔር *ሥ*ልጣን ጠላት ነው።
   ሐ. ከ*ሥጋ* የሆነ ነገር ሁሉ የእግዚአብሔርን ዙፋን ይጻረራል፤ በእግዚአብሔር ዓላማ ላይ እንቅፋት እንዲሆንም ስውር ተንኮለኛው፣ የእግዚአብሔር ጠላት የሆነው ሰይጣን ይጠቀምበታል—2 ቆሮ. 2፡11።

ሠ. *ሥጋ* ንግሥናን ይጻረራል፦

1. *ሥጋ* ባለበት የእግዚአብሔር መንግሥት ሊኖር አይችልም።
2. ስለዚህ ምክንያት የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣት ከመቻሉ በፊት *ሥጋ* ሙሉ በሙሉ መወገድ አለበት።

## III. በ 1ኛ ሳሙኤል 15፡2 እስራኤልን ሲዋጉ በእስራኤል ላይ ላደረጉት ነገር አማሌቃውያንን እንደሚቀጣ ያሕዌ አወጀ፡-

ሀ. የእስራኤል ልጆች ወደ እግዚአብሔር ግብ ለመድረስ ሲጓዙ ሳሉ አማሌቅ የእስራኤልን ልጆች ተዋጋ—ዘጸ. 17፡8-16፤ 1 ሳሙ. 15፡2-3፡-

1. በዘጸአት 17፡8-16 ላይ በተገለጸው ከአማሌቅ ጋር በነበረው ጦርነት ሙሴ የእግዚአብሔርን በትር በእጁ ይዞ በተራራው ጫፍ ላይ ቆመ፣ ኢያሱም ከተመረጡ ሰዎች ጋር አማሌቅን ለመዋጋት እና ለማሸነፍ ወጣ።
2. ኢያሱ ሲዋጋ ሳለ ሙሴ ይጸልይ ነበር።
3. ኢያሱ አማሌቅን ካሸነፈ በኋላ እግዚአብሔር "የእግዚአብሔር ሰልፍ በአማሌቅ ላይ ለልጅ ልጅ ይሁን አለ" (ቁ. 16)፤ እግዚአብሔር በአማሌቃውያን ምክንያት የተፈጠረውን እንቅፋት ምን ያህል አክብዶ እንዳየው ይህ ያሳያል።

ለ. ዘጸአት 17፡8-13 አማሌቅን እንዴት መዋጋት እንዳለብን ያሳያል፡-

1. በሚማልደው ክርስቶስ እና በሚዋጋው መንፈስ አማሌቅን እንዋጋለን—ሮሜ 8፡34፤ ዕብ. 7፡25፤ ገላ. 5፡17፡-
   ሀ. ሙሴ በተራራው ጫፍ ላይ እጁን ማንሣቱ የዐረገው ክርስቶስ በሰማያት እንደሚማልድ በምሳሌ ያሳያል—ዘጸ. 17፡9፤ 11።
   ለ. ኢያሱ አማሌቅን መዋጋቱ በውስጣችን የሚያድረው መንፈስ ሥጋን መዋጋቱን በምሳሌ ያሳያል—ቁ. 9፤ 13።
   ሐ. ከሚዋጋው መንፈስ ጋር ለመተባበር ከሚማልደው ክርስቶስ ጋር መጣመር ያስፈልገናል—ቆላ. 3፡1-3፣ 5፤ ሮሜ 8፡34፣ 13፤ ገላ. 5፡24፣ 17።
2. ከአማሌቅ ጋር ባለው ውጊያ በመጸለይ እና ሥጋን በመግደል ከጌታ ጋር መተባበር ያስፈልገናል—ሉቃ. 18፡1፤ 1 ተሰ. 5፡17፤ ሮሜ 8፡13፤ ገላ. 5፡24፡-
   ሀ. ስንጸልይ ከሚማልደው ክርስቶስ ጋር አንድ ነን—ሮሜ 8፡34።
   ለ. ሥጋን ስንገድል ከሚዋጋው መንፈስ ጋር አንድ ነን—ገላ. 5፡17።
   ሐ. በአንድ በኩል ከክርስቶስ ጋር መጸለይ አለብን፤ በሌላ በኩል በሚዋጋው መንፈስ ሥጋን መግደል አለብን—ቁ. 24።
   መ. አሮጌውን ሰው መስቀል የእግዚአብሔር ኃላፊነት ነበር፤ ሥጋን መስቀል የእኛ ኃላፊነት ነው—ሮሜ 6፡6፤ 8፡13፤ ገላ. 5፡24።

## IV. እግዚአብሔር ሳኦልን "አማሌቅን ምታ" እና "ያላቸውንም ሁሉ ፈጽመህ አጥፋ፥ አትማራቸውም" ብሎ አዘዘው፣ ሳኦል ግን ለያሕዌ አልታዘዘም—1 ሳሙ. 15፡3-9፡-

ሀ. ሳኦልም አማሌቃውያንን ገደለ፣ ነገር ግን ለንጉሥ አጋግ፥ ለተመረጡትም በጎችና በሬዎች፣ ለሰቡትም ጥጆችና ጠቦቶች፥ ለመልካሞቹም ሁሉ ራራላቸው—ቁ. 7-9።

ለ. ሙሉ በሙሉ ሊያጠፉ ከሚገባቸው ነገሮች ምርጦቹን ሳኦልና ሕዝቡ ማስቀረታቸው በልምምድ የሥጋችንን፣ የተፈጥሯዊ ሕይወታችንን መልካም ገጽታዎች እንደ ወድ መዝገብ እንደምንይዝ ያሳያል፡-

1. ከእግዚአብሔር ጸጋ ውጭ እና በእግዚአብሔር ላይ ከመደገፍ እና በእርሱ ላይ ከመታመን ውጭ የምናደርገው ነገር በሙሉ ከሥጋ ነው—ፊልጵ. 3፡3-4።
2. እያንዳንዱ የሥጋ ገጽታ፣ መልካም ይሁን ክፉ፣ ጸጋንና የእግዚአብሔርን መንግሥት ይቃወማል፣ ክርስቶስንም እንዳንደሰት ያደርጉናል፤ ስለዚህ የሥጋን እያንዳንዱ ገጽታ መጥላት እና ሥጋን በማጥፋት ፍፁም መሆን አለብን—ሮሜ 8፡13፤ ገላ. 3፡3፤ 5፡2-4።

ሐ. እግዚአብሔር ሳኦል ከከብቶቹ የተመረጡትን እንደ መሥዋዕት እንዲያቀርብለት አልፈለገም—1 ሳሙ. 15፡15፡-

1. ሥጋ ምንጩ የሆነ ማንኛውም ለእግዚአብሔር የሚቀርብ እና የሚሠዋ ነገር በእግዚአብሔር ዓይን ክፉ ነው—ቁ. 19።
2. በገዛ ፈቃዳችን መሠረት የሆነን ነገር ለእግዚአብሔር ማቅረብ ድፍረት ነው፣ ኃጢአትም ነው—ዘፍ. 4፡5፤ ማቴ. 7፡22-23።

## V. በገዛ ፈቃዳችን መሠረት መልካም ነገር ማድረግ በእግዚአብሔር ዙፋን ላይና በእርሱ ኢኮኖሚ ላይ የአመፅ ድርጊት ነው—1 ሳሙ. 15፡22-23፤ ዘጸ. 17፡16፡-

ሀ. የሳኦል አለመታዘዝ በእግዚአብሔር ላይ አማፂ እና የእግዚአብሔር ጠላት እንደሆነ አጋለጠው—1 ሳሙ. 22፡17።

ለ. ሳኦል በእግዚአብሔር ላይ ፈጽሞ አመጸኛ ነበር፤ ለእግዚአብሔር ምንም አይነት መገዛት አልነበረውም፣ እግዚአብሔርንም እንደ ንጉሡ እና እንደ ራሱ አልወሰደም።

ሐ. ሳኦል ጣዖታትን የማምለክ ያህል በሆነው በአመፅ ተቀናብሮ ነበር—15፡23።

መ. ሳኦል ያደረገው ነገር የእግዚአብሔርን ውጥን ሳይሆን የክፉ መንፈስን ውጥን ለማከናውን፣ ክፉ መንፈስን የመገናኘት ያህል ክፉ ነበር—ቁ. 23።

ሠ. አመፅ ሁሉ በድፍረት የመሄድ ጉዳይ፣ ያለ እግዚአብሔር ነገሮችን ለማድረግ የመድፈር ጉዳይ ነው።

## VI. ሳኦል አማሌቅን ፈጽሞ ስላላጠፋ ንግሥናውን አጣ—15፡26፣ 28፡-

ሀ. *ሥጋ*ችን በማስወገድ ፍጹም ካልሆንን፣ እኛም እንደ ሳኦል ንግሥናችንን እናጣለን—1 ጴጥ. 2፡9፤ ራእ. 1፡6፤ 5፡10።

ለ. የሳኦል የአመፅ ታሪክ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ በ*ሥጋ*ችን ምንም ነገር ማድረግ እንደሌለብን ማስጠንቀቂያ ነው፤ በሁሉ ነገር *ሥጋ*ችንን መስቀል እና በመንፈሳችን ውስጥ የሚያድረውን ሕይወት የሚሰጥ፣ የተጠናቀቀ መንፈስ የሆነውን እና ከእኛ ጋር አንድ የሆነውን ጌታ ለመከተል በታማኝነት መንፈሳችንን ማንቀሳቀስ አለብን—1 ቆሮ. 15፡45፤ 6፡17፤ 2 ጢሞ. 4፡22፤ ገላ. 5፡16፣ 25።

ሐ. አማሌቅ ሲወገድ የእግዚአብሔር መንግሥት ወዲያውኑ ይመጣል—ዘጸ. 18፡1-26፡-

1. የእግዚአብሔር መንግሥት ሁሉ ነገር ለእግዚአብሔር የተገዛበትን የእግዚአብሔርን ሥልጣን ያመለክታል—ማር. 1፡15፤ ዮሐ. 3፡3፣ 5፤ ራእ. 11፡15፤ 12፡10፤ ዳን. 2፡44።
2. *ሥጋ* ንግሥናን ስለሚጻረር የእግዚአብሔር መንግሥት ከመምጣቱ በፊት *ሥጋ* ሙሉ በሙሉ መወገድ አለበት—1 ቆሮ. 6፡9-10፤ ኤፌ. 5፡5።

መ. *ሥጋ*ን ፈጽሞ ለማጥፋት የጌታን ቃል ከተከተልን እና በመንፈስ መሠረት ከኖርንና ከተመላለስን ንግሥናው ይኖረናል፣ በእግዚአብሔር መንግሥትም ውስጥ እንሆናለን—ሮሜ 8፡4፤ 14፡17፤ ገላ. 5፡19-21፤ 2 ጴጥ. 1፡5-11።

*© 2021 Living Stream Ministry*